## ሙት (MUT) ምንድን ነው?

ሙት ለመካከለኛውና የታችኛው ፍራንኮኒያ አስተዳደር አድሎዋዊነትን በተመለከተ የምክር አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው። ቩርዝቡርግ፣ ኑርንበርግ፣ ሽቫይንፉርት እና በሌሎችም አካባቢዎች ለሚኖሩ ሰዎች የምክር አገልግሎት እንሰጣለን

የምክር አገልግሎታችንን የምንሰጠው፡-

- ከክፍያ ነጻ
- በሚስጥር
- እንዳስፈላጊነቱ ከአስተርጓሚ ጋር
- የተጎጂውን መብት ለማስጠበው ባለመ መልኩ
- ከምንም ዓይነት ተጽዕኖ ውጪ ነው

አድሎዋዊነት ደርሶብዎት ከሆነ ያነጋግሩን:-

ኢሜይል፡- kontakt@beratung-mut.de

ስልክ፡-01523-6777012 (በጀርመንኛና እንግሊዝኛ)

## አድሎዋዊነት ምንድን ነው?

በርካታ ሰዎች ያለምንም በቂ መሰረታዊ ምክንያት፤ የሆነ ቡድን አባል ናቸው ወይም ሊሆኑ ይችላል ከሚል መነሻ ግምት በመነሳት ብቻ በተለየ መልኩ ወይም ጥሩ ባልሆነ መልኩ ሊስተናጋዱ ወይም አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ።

ሁሉም የሰው ልጆች በዕኩል ሊስተናገዱ ይገባቸዋል የሚለው የሕግ ማዕቀፍ (AGG) ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሚመጡ መድሎአዊነትን ለመከላከል ያገለግላል፡-

- የብሄር ማንነት
- ጾታ
- ሐይማኖት/ዕምነት
- የአካል ጉዳተኝነት
- ዕድሜ
- ጾታዊ ማንነት

አንድ ሰው ያለምንም በቂና አሳማኝ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ከተደረገ አድሎዋዊነት ተፍጸሞበታል ተብሎ ይወሰዳል።

ሁሉም የሰው ልጆች በዕኩል ሊስተናገዱ ይገባቸዋል የሚለው የሕግ ማዕቀፍ ከዘረዘራቸው የአድሎዋዊነት አይነቶች ውጪ በሆኑ ጉዳዮች፤ ለምሳሌ በሰዎች ተፈጥሮአዊ ማንነታቸው፣ በሰውነት ክብደታቸው፣ በብሔራቸው ወይም ማሕበራዊ ማንነታቸውና ባላቸው የሐብት መጠን የተነሳ መድልዎ ሊፈጸምባቸው ይችላል።

Ein Förderprogramm der
respekt*land Antidiskriminierungsberatung für ganz Deutschland
Antidiskriminierungsstelle des Bundes

M&T
Beratung gegen Diskriminierung

ከዚህ ቀጥሎ ጥቂት የመድሎዋዊነት መገለጫ ምሳሌዎችን ማየት ይቻላል፡-

- አንድ ሴት ቢሮ ውስጥ የጾታ ትንኮሳ ከተደረገባት
- አንድ ሰው በዘረኝነት የተነሳ ወደ ዲስኮ እንዳይገባ ከተከለከለ
- አንድ የስራ ቅጥር ማስታወቂያ ያለበቂ ምክንያት "ወጣቶችን„ ብቻ ለመቅጠር እንደሚፈልግ የሚገልጽ የስራ ቅጥር ማስታወቂያ ቢያወጣ
- አንድ ሰው ስሙ "የጀርመን ሥም" ስላልመሰለ ብቻ የቤት ኪራይ እንዳያገኝ ከተደረገ
- አንድ የአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪ የሚጠቀም ሰው በስራ ቅጥር ጊዜ የአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪ መጠቀሙ በስራው ላይ የሚያደርሰው ምንም አይነት ችግር እንደሌለ እየታወቀ ስራውን እንዳያገኝ ከተደረገ
- አንድ ሆቴል ሁለት ጌይ ወንዶችን ክፍል አላከራይም ካለ

አድሎዋዊነትን በተለያይ መንገድ መከላከል ይቻላል። በምክር አገልግሎታችን ወቅት ከዕርስዎ ጋር በጋራ ሆነን ለእርስዎ የሚስማማዎትን አይነት አማራጭ እንፈልጋለን።